دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

# ዓለማቀፍ መቻቻል

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae zhic
800 555 اتصل على JUST CALL
P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E
www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

መቻቻል ዛሬ ላይ የማህበረሰቦች ባህላዊ፣ ሐማኖታዊ እና ጎሳዊ ሰብኣዊ ባህሪዎች ብዝሃነት መስፋፋቱ አስፈላጊነቱ እየጨመረ የሚሄድ ዓለምአቀፍ ፍላጎት ሆኗል። የመቻቻል እሴቶች ይበልጥ እየበዙ እና ክበባቸውን ባሰፉ ቁጥር በዓለም ላይ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል አለመግባባት፣ አላስፈላጊ ግጭትና ንትርክ እየቀነሰ ይሄዳል። የዓለም የመቻቻል ሥዕል ሊሟላ የሚችለው የመቻቻልን ፅንሰ-ሀሳብ በማስፋት ሁኔታ ውስጥ… ባህላዊ፣ ሐይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ በማካተት ብቻ ነው። ስለሆነም የሰላም፣ የመቻቻልና የህብረተሰብ አብሮ መኖር እሴቶችን ማጠናከሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፍሬ እንዲያፈራ መቻቻልን በቀጠናው ለመተግበር የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል። የዓለምአቀፍ ስምምነቶች፤ ዓለምአቀፋዊ መቻቻልና በማህበረሰቦች ውስጥ ሰርጾ እንዲገባ ይጠይቃሉ። በተለይም በዩኔስኮ እ.ኤ.አ. በ1995 ዓ.ል የተቀበሏቸው መርሆዎች "መቻቻል ማለት፤ ለዓለማችን ባህሎች የበለፀጉ ብዝሃነቶች፣ የአመለካከት ዓይነቶችና ሰብአዊ ባህሪያችን፣ መቀበልና አድናቆትን ማክበር ማለት ነው።" በዚህ መሠረት መቻቻል ግለሰብን ዓለምአቀፋዊ ዜጋና በየትኛውም ቦታ ህይወት ቀጥተኛና ገር እንድትሆንለት ያደርጋል።

ሁለንተናዊ የመቻቻልን መርህ ለማሳካትና የሰብአዊ እሴቶቹ ተግባራዊነት በዋነኝነት የሚመነጨው በመጀመሪያ ከሰው እምነት፣ አስተሳሰብና ህሊና ነው። ከዚያም በተግባር በማጠናከርና በአይን እማኝነት በማረጋገጥም ነው። ነገር ግን ሃቅን የብቻ ከማድረግና የሌሎችን መብት ከመንጠቅ በመራቅና በመቆጠብ መሆን አለበት። የሰው ልጆች የአስተሳሰብና የትችት ተሰጠኦዎች እንደተፈጠሩበት አካላዊ እና ሥነ ምግባራዊ ባህሪዎች ይለያያሉ። የተባረከው አሏህ ቃልም ይህንን ያመላክታል፡- (ጌታህ ቢሻ ኖሮ የሰው ልጅን አንድ ህዝብ ባደረገ ነበር። ግና [ይህን ማድረግ አልፈለገም]። እናም ምንጊዜም ከመወዛገብ አይድኑም። አሏህ ያዘነላቸው ሲቀሩ።) [ቅዱስ ቁርዓን ምዕ፡- 11 ቁ. 118_119]. ይህ የሆነበት ምክንያት፤ ብዝሃነትና ልዩነት የግኝትና የፍጥረት መሠረታዊ ዓላማና ግብ ነው ስለሆነ ነው። ብዝሃነትና ልዩነት ለሰው ልጆች ድልብ ሃብት፣ የብልጽግና እና የልቅና መንገድም ነው። ዓለምአቀፍ የመቻቻል

ባህል ትግልና ጥረትን በማፍሰስ እንዲሁም የህዝቦች የመግባባትና የመናበብ መለኪያም ነው። ስምምነትና መላመድ የተንሰራፋበትን ዓለማቀፋዊ ማህበረሰብንም ይገነባል። በዚህ መልኩም የጥበብ ድምጽ ከሁሉም በላይ ከፍ ብሎ ይደመጥበታል። እንዲሁም የሰው ልጅ ለባልንጀራ ወንድሙ ያለው ታማኝነት ያለ አድልዎ እና ያለ ልዩነት ይታያል።

በመላው ዓለም ዙሪያ ያሉ የሰው ልጆች ባህላዊ ብዝሃነት የሰለጠነ ውህደት እውነታ እንጂ ሌላ አይደለም። ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት እና ማህበረሰቦቻቸውን ለማጎልበት እርስ በእርስ የተሰባጠረ ነው። የሰዎች ልዩነት ምንም ይሁን ምን፤ የሰው ልጅ እያንዳንዱን ማህበረሰብ ከሌሎች ጋር በሚለየው ነገር ለመተባበር፣ ለማጋራት እና ተጠቃሚ ለማድረግ ሰፋፊ አካባቢዎች እንዲኖሩት ያስችለዋል። በቁጥሩ ውስጥ የተካተቱትን የፍጥረትን ብዝሃነት ስፋት እና ብዛት ልዩነቶችን የሚያጠና ማንኛውም ሰው፤ በቅዱስ ቁርዓን አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሰው ይህን በጎ ሥራ እንዲሠራ ያደርገዋል፦ (የሰማያትና የምድር መፈጠር፣ ቋንቋችሁና ቀለማችሁም መለያየቱ ከተዓምራቱ ነው።) [ቅዱስ ቁርዓን ምዕ፦ 30 ቁ. 22]. በተጨማሪም የሰው ልጆችን ለማገልገል በዓለም ህዝቦች መካከል መልካምና ገንቢ የሆነ መስተጋብር ለማድረግ ያነሳሳል። በዓለም ማህበረሰብ ውስጥ የመቻቻል መሠረቶችን በመጣል፤ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃዎች እንዲጠናከር ይጠይቃል። በተለይም ዛሬ ያለው ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ የጤንነት፣ የደስታና የኑሮ ጥራት መንስኤዎችን ለማራመድ የመቻቻል እሴት አስፈላጊነት በግልጽ የሚያንፀባርቅ ነው። ይህም የሰው ልጆች በሙሉ ያለምንም ልዩነት የሚፈልጉት መሠረታዊ ጉዳይ ነው።